# መለስ ለምን ስልጣኑን መልቀቅ ፈለገ?

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መለስ ዜናዊ ከፖለቲካ እና ከመንግስት ስልጣን እንደሚለቅ በተደጋጋሚ ገልጿል:: በዚህ የመለስ ውሳኔ ላይ ጊዜ ሰጥቶ መወያየቱ ለተቃዋሚ ቡድኖች ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል ግምት አለኝ:: በመለስ ስልጣን መልቀቅ ዙሪያ ሶስት እንድምታዎች ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ቅርብ በሆኑ ተችታኞች እየተስተናገዱ ነው::

አንደኛው አምባገነን ባህሪያቶቹ በፍጹም ስለማይፈቅዱለት ስልጣን አይለቅም:: በራሴ ፍላጎት ሳይሆን በፓርቲዬ አስገዳጅነት ነው ስልጣን ላይ የቆየሁት የሚል እና ሃያላን መንግስታትን ማሳመኛ ዘዴ ነው የሚል ነው:

ሁለተኛው ደግሞም ስልጣኑን ሊለቅ ይችላል ሆኖም ግን ከመጋረጃ ጀርባ የፑቲን አይነት ዘዴ በመጠቀም ድርጅቱን እና መንግስትን ያስተዳድራል የሚል ነው::

ሶስተኛው ደግሞም የመለስን ንግግር ከሚያምኑ የዋሃን የሚመደቡት እና ስልጣኑን ይለቃል ፤ በፓርቲው ላይም የአንበሳ ሳይሆን የተከበረ እና ተደማጭ ድርሻ ይኖረዋል የሚል ነው::

ራሴን እንደ የዋህ ባልቆጥርም የምስማማው በሶስተኛው ግምት ላይ ነው:: የምስማማው መለስን በማመን ሳይሆን አለማመኑ ለተቃዋሚ ግንባር እና ፓርቲ እንደዛ ብሎ ማሰቡ ፖለቲካዊ ጥቅም ስለሚኖረውም ነው:: አዎ መለስ ስልጣን ይለቃል የኢህአዴግም ሊቀ-መንበር አይሆንም:: ለምን?

የህወሃትን ባህሪ ስንመረምር አራት አበይት የባህሪ እና የፖለቲካ ስልት ልውውጦች እናገኛለን:: ህወሃት ሲመሰረት አላማዬ ብሎ የተነሳው የትግራይ ህዝብን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስርአት ለመመስረት ብሎም ለመገንጠል ነው:: ሆኖም ከጥቂት አመታት በኃላ ትግራይ ተገንጥላ የትም እንደማትደርስ ብሎም የትግራይ መገንጠል ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ሲረዱ መገንጠልን ትተው በብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መመስረት ተድርጎ የህወሀት የትግል ስልት ተቀረጸ:: ሁለቱ አበይት ለውጦች የተከሰቱት ህወሃት የአልባንያ ስታይል ሶሻሊዝምን እያቀነቀነ ነበር::

ሶስተኛው ለውጥ ደግሞም በአለም ላይ እየጠፋ የመጣውን ሶሻሊዝምን መከተል የትም እንደማያደርስ በመረዳት ዲሞክራሲያዊ ግንባር መሆን ነው:: በአጭር ጊዜ እና በሚገርም ፍጥነት ራሱን ከሶሻሊዝም ያነጻው ኢህአዴግ እርምጃው ውጤታማ አድርጎታል::

አራተኛው ለውጥ እና ክፉኛ ህወሃትን የጎዳው እና አቅሙን ያዳከመው ደግሞም በሉአላዊነት ጉዳይ በተነሳ ጸብ የኢህአዴግ ውስጣዊ ተሃድሶ ነው:: የቤተ-መንግስት ቡድን የተባለው እና የእነ ተወልደ ቡድን ህወሃትን የመቆጣጠር ብሎም የመቀየር ትግል የተደመደመው በመለስ ዜናዊ የቤተ-መንግስቱ ቡድን ነው:: በወቅቱም «ቦናፓርቲዝም» የሚል ወፈር ያለ ማብራሪያ በመለስ ዜናዊ ለፓርቲው የውስጥ ሰዎች ተሠጥቶ ነበር::

አራቱም ለውጦች በመለስ ዜናዊ የተቀየሱ እንዲሁም የተተገበሩ ናቸው:: አራቱም ለውጦች ወቅቱን ያገናዘበ ኢህአዴግ/ህወሃትን ከመበስበስ እና ከመውደቅ ያዳነ ነው:: ይህን የምለው መለስን በመደገፍ ሳይሆን መለስ በወሳኝ ወቅት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ምን ያህል ጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ እንዳመጡለት ለማሳየት ነው::

ከምርጫ 97 በኃላ ኢህአዴግ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል:: የግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ህግ፤ የፕሬስ እና የጸረ-ሽብር ህግ እንዳሉ ሆነው ፤ የባንዴራ ቀን፤ በሚሌኒየም ስምም የህዝብን ቀልብ ለመሳብ ተሞክሯል:: አምስተኛው እና የጊዜው ለውጥ ደግሞም ኢህአዴግን የትግራይ ተወላጅ ባልሆነ እና የትጥቅ ትግሉን ባልቀመሰ ትኩስ ሀይል መምራት ነው::የምርጫ 97 በኢህአዴግ ላይ ካመጣው ጉዳት ለመዳን የመለስ ዜናዊ ስልጣን መልቀቅ ለኢህአዴግ ትልቅ ድል የሚያስገኝ ስትራቴጂ እንደሆነ በራሱ በመለስ ዜናዊ የታሰበበት እንደሆነ እገምታለሁ::

አንደኛ ኢህአዴግን ከህወሃት ነጥለው ማየት ያቃተቸውን አብዛኛውን ያለማጋነን ሁሉንም የኢትዮጵያን ህዝብ ይህንን አመለካከት ለማስወገድ ጥሩ መንገድ ነው ተብሎ ታስቦበት ይሆናል:: የትግሬ ጠ/ሚር እና ሊቀመንበርን አለማስቀመጥ በህዝቡ ዘንድ የግንዛቤ ለውጥ ያመጣል የሚል አመክንዮ ይኖረዋል::

ሁለተኛ የኢህአዴግን አመራር በኦሮሞ ተወላጅ መተካት እስካሁን ድረስ የመብት ጥያቄው ያልተመለሰለት እና አኩርፎ ያለውን የኦሮሞ ህዝብ በአንድ ውሳኔ እና አንድን ግለሰብ ከስልጣን በማውረድ ደጋፊ ለማድረግ የታቀደበት እርምጃ ነው ብዬ አስባለሁ:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከትግራይ ተወላጆች በተለየ በትጥቅ ትግሉ ለረዥም ጊዜ የተሳተፉት የአማራ ታጋዮችንም ስልጣን ላለማስቀመስ ይህ ዘዴ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: በተጨማሪም በብአዴን ውስጥ ብቃት ያለው ሰው ጎልቶ ስለማይታይ ከብአዴን አዲስ ጠ/ሚር ይወጣል የሚል እምነት የለኝም::

ሶስተኛ መለስ ዜናዊ ለታሪክ ግድ የሌለው ሰው አይደለም:: መለስ ዜናዊ እንደ ግለሰብ ታሪክ መስራት ይፈልጋል:: የብዙ ፖለቲከኞች የመጨረሻ ግብ አገርን መቀየር ብቻ ሳይሆን በታሪክ ውስጥ የአንበሳ ድርሻ መያዝ ነው:: ፖለቲከኛ አገር ወዳድ ብቻ ሳይሆን ታሪክ ወዳድም ነው:: ታሪክ ደግሞም ለአውራ እንጂ ለተከታዮች እምብዛም ግድ የላትም:: ስለዚህም መለስ የታሪክ አውራ በሆነበት በዚህ ወቅት ከተቻለ ከዳግማዊ ምንሊክ በበለጠ አለያ ደግሞም የሚመጣው ትውልድ በቀና መንገድ የሚዘክረውን ተግባር መፈጸም ይፈልጋል:: ከዚህ አንጻር ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የመጀመሪያው መግዛት እየቻለ ስልጣን በቃኝ ያለ ኢትዮጵያዊ መሪ ተደርጎ በታሪክ በጎ ገጽ መጻፍ ይፈልጋል-ሌሎች አከራካሪ ስራዎቹ እንዳሉ ሆነው::

አራተኛ መለስ የኢህአዴግ ጉዞ የሚፈልገውን ያህል ሊሄድለት ስላልቻለ ቦታውን ለሌሎች ለመልቀቅ ይፈልግ ይሆናል::

እኒህ ከላይ የተጠቀሱትን አራት አመክንዮች የሌሎች ሰዎች ሀሳቦችም ተጨምረውበት ተቃዋሚ ፖለቲከኞች እና ግንባሮች የማይዳከሙበትን የፖለቲካ ስልት ይቀይሳሉ የሚል ግምት አለኝ::

መለስ ዜናዊ ስልጣኑን አይለቅም የዋህ አትሁኑ ብሎ ቅስቀሳ ማድረግ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ለተቃዋሚዎች የሚጨምርለት ፖለቲካዊ ይሁን ድጋፋዊ ትርፍ የለውም ብሎ ያምናል:: በተቃራኒው ደግሞም የመለስ አዲሱ ስትራቴጂ ኢህአዴግን ትርፋማ ምናልባትም በኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ የማይነካ ጠንካራ ፓርቲ አድርጎ ሊያዘልቀው ይችላል:: ከዚህ አንጻር እና ከፖለቲካዊ ስልት አኳያ ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ ደረጃ ያደርሷታል ተብለው የሚታሰቡ ፖለቲካዊ ቡድኖች የትግል ስልት ይቀይሳሉ የሚል እምነት አለኝ::

branaethio@yahoo.com